የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ – ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 50
ADDIS ABABA– 20th May, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፱/፲፱፻፺፩ ዓ·ም
እ·ኤ·አ· ፲፱፻፺፰ ከፊል የወለድ ክፍያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ....... ገጽ ፩ሺህ፳፫

## CONTENTS

Proclamation No. 169/1999
African Development Fund Loan Agreement for Financing Part of the 1998 Interest Payment Ratification Proclamation ................................................ Page 1023

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፱/፲፱፻፺፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለወሰደው ብድር እ·ኤ·አ· በ፲፱፻፺፰ መከፈል ካለበት ወለድ ውስጥ የከፊሉን ክፍያ ለመፈጸም መጠኑ ዩ·ኤ· ፯ ሚሊዮን ፯፻፹፮ሺህ (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ·ም በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንን የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ “እ·ኤ·አ· ፲፱፻፺፰ ከፊል የወለድ ክፍያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፱/፲፱፻፺፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 169/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 7,786,000 UA (seven million seven hundred and eighty six thousand Units of Account) for financing part of the 1998 interest payment due to the African Development Bank by the government of Ethiopia, was signed in Abidjan on the 12th day of February, 1999;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 20th day of May, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the ''African Development Fund Loan Agreement for financing part of the 1998 interest payment Ratification Proclamation No. 169/1999.''

ያንዱ ዋጋ
Unit Price ብር 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O. Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ “የብድር ስምምነት” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢ·ቲኤች/ኤስኤፍኤም/ ፺፱/፵፫ የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ·ኤ· ፯ ሚሊዮን ፯፻፹፮ሺ (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ዩኒትስ አፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation ''Loan Agreement'' means the Loan Agreement No. F/ETH/SFM/99/43, signed in Abidjan on the 12th day of February, 1999 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of UA 7,786,000 (seven million seven hundred eighty six thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 20th day of May, 1999.

Done at Addis Ababa this 20th day of May, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL

DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE